# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት


የሰበር መ/ቁ/218284

ሰኔ 02 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ

ተጠሪ/ዎች፡- 1ኛ/ ወ/ሮ አስረሳሽ ከተማ

2ኛ/ አቶ አዱኛ አንደሞ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የብድር ውል የሚመለከትነዉ፡፡ክርክሩ የተጀመረው በደቡብ ምዕራብ ኢ.ት/ሕ/ ክልል ሸካ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ከሳሽ በመሆን በአሁኑ ተጠሪዎች ላይ ባቀረበችው ክስ ተጠሪዎች ከአመልካች ባንክ ጋር ሚያዚያ 17 ቀን 2011 ዓ.ም በገቡት የብድር ውል በተወሰነ ጊዜ የሚከፈል ብር 800,000 ብድር አከፋፈሉን አስመልክቶ በዋናው እዳ ላይ በአመት 16.75% የሆነውን አመታዊ ወለድ በየሶስት ወሩ ብር 86,173 እየከፈሉ በሚያዝያ 17/2014 ዓ.ም ለማጠናቀቅ እና በውሉ ላይ የተመለከተው ጊዜ መሰረት ክፍያውን ካልፈፀሙ ያልተከፈለውን እዳ ከ3%መቀጮ ጋር ለመክፈል ተስማምተዋል፡፡ተጠሪዎች ከህዳር 17/2012


ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ዓ.ም ጀምሮ ክፍያውን ያቋረጡ በመሆኑ ተከሳሾች በአንድነትና ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ዋና እዳ፣ ወለዱንና መቀጮውን ጨምሮ ብር 896,715 እንዲከፍሉ ይወሰንልን የሚል ዳኝነት የጠየቀ መሆኑን የ1ኛ ተጠሪ መልስ ለባንኩ በግልጽ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን በዋስትና የያዘውን ንብረት ያለምንም መደበኛ ክስ ሂደት ብድሩ ሳይከፈል በሚቀርበት ጊዜ በጨረታ በመሸጥ ወይም ገዥ ካልቀረበ ንብረቱን መረከብ እየቻለ ይህንን ሳያደርግ ወይም ይህንን ለማድረግ ያልቻለበትን ምክንያት እስካልገለጸ ድረስ ጉዳዩን ለመደበኛ ፍ/ቤት የሚያቀርብበት የህግ ምክንያት አይኖርም፡፡ብድሩ ተከፍሎ የሚጠናቀቅበት ጊዜ ሚያዝያ 17/2014 ዓ.ም በመሆኑ ብድሩን ከፍሎ የማጠናቀቂያ ጊዜ ያልደረሰ በመሆኑ የመክፈያ ጊዜው ሳይጠናቀቅ ክስ የማቅረብ መብት የለውም በማለት የመጀመሪያ መቃወሚያ ማቅረቡን 2ኛ ተጠሪም እዳዉ የ1ኛ ተጠሪ የግሏ መሆኑን ስላረጋገጠች እና 2ኛ ተጠሪ በተከሳሽነት የሚሳተፍበት የህግ አግባብ የለም በማለት መቃወሙን መዝገቡ ያሳያል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ክርክር በመስማት ጉዳዩን መርምሮ አመልካች (ባንክ) በአዋጅ ቁጥር 97/1990፣98/1990 እና 216/1992 መሰረት በተሰጠው ስልጣን ብድር ሲያበድር በዋስትና የያዘውን ንብረት ያለምንም መደበኛ የክስ ሂደት ብድሩ ሳይከፈል በሚቀርበት ጊዜ በጨረታ በመሸጥ ብድሩን ማስመለስ የሚችል እና ገዥ ካልቀረበ ንብረቱን መረከብ እየቻለ በመያዣ የያዘውን ንብረት በመሸጥ ወይንም በመረከብ ብድሩን ለማስመለስ ያልቻለበትን በቂ ምክንያት እስካልገለፀ እና በአዋጅ የተሰጠውን ሥልጣን ቀድሞ ሳይጠቀም ጉዳዩን ለመደበኛ ፍርድ ቤት የሚያቀርብበት የህግ አግባብ አይኖርም፡፡በተጨማሪም አመልካች የብድር መክፈያ ጊዜ ከማለቁ በፊት ወይንም የመክፈያ ጊዜው ያለፈውን ብቻ ለይቶ ባላቀረበበት ሙሉ ብድሩን በሚመለከት ክስ የማቅረብ መብት የለውም፤ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ ተበዳሪ ወይም ዋስ ባልሆነበት የተበዳሪ ባል በመሆኑ ብቻ በክሱ ውስጥ መካተቱ የህግ አግባብነት የለውም በማለት ክሱን በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 245(2) መሰረት በብይን ዘግቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለደቡ/ምዕ/ኢ/ሕ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ጉዳዩ አያስቀርብም በማለት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት ዘግቶታል፡፡

አመልካች ብይኑን በመቃወም ያቀረበውየሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ፡- ተጠሪዎች ከዚህ በፊት ለአሁኑ አመልካች በዋስትና ካቀረቡት ንብረቶች ውስጥ አንዱ የካርታ ቁጥር 3625/493/2000 የሆነው ቤት ላይ አመልካች የመያዣ መብት የለውም በማለት የስር ፍ/ቤት በመ/ቁ. 14779 ላይ ካርታው ለተጠሪዎች እንዲመለስላቸው በሰጠው ውሳኔ መሰረት ንብረቱ ከመያዣ ውጭ ሆኖላቸዋል፤ ሌላኛው የካርታ ቁጥር 9610/758/08 በብድር ዋስትና የተያዘው ቤት በእሳት

ተቃዋሎ ከአገልግሎት ውጭ ሆኗል፣በዚህ ምክንያት በዋስትና የተያዘው ንብረት በጨረታ መሸጥ ወይም መረከብ አንችልም በማለት በበቂ ምክንያት አስረድተን እያለ የስር ፍ/ቤት በቅድሚያ በአዋጅ በተሰጣችሁን አልተጠቀማችሁም በማለት በመቃወሚያ ክሳችን ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽመዋል፡፡በተጨማሪም አዋጅ 97/90፣98/90 እና 216/92 ባንኮችን የተሻለ መብት ለማጎናፀፍ እንጂ መብታቸውን የሚያስተጓጉል ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም መያዣው እዳውን አይሸፍልኝም የሚል ስጋት ካጋጠመው በፍርድ ቤት ክስ እንዳይመሰረቱ የሚከለክላቸው የህግ ድንጋጌ የለም፡፡የብድር እዳው የሚከፈለው በአንድ ጊዜ ሳይሆን በየ3(ሶስት) ወሩ ስለመሆኑ ከብድር ውሉ በግልጽ የሚታይ ሲሆን ተጠሪዎች በውሉ መሰረት የየወቅቱን ክፍያ ካቋረጡና ብድሩ በተበላሸ ብድር የሚመደብ(bad debt) ውስጥ ከገባ አመልካች የመጨረሻውን የውል መፈፀሚያ ጊዜ ለመጠበቅ ሳይገደድ አስቀድሞ ገንዘቡ እንዲከፈል የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑን፣የስር ፍ/ቤት ግን ክፍያው በአንድ ጊዜ እንዲከፈል እንደተስማሙ በመቁጠር የውል መፈፀሚያ ጊዜ ሳይደርስ ክስ ማቅረብ አግባብነት የለውም በማለት ክሱን ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ እንዲታረም በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት አመልካች በባንክ አዋጆች መሰረት መያዣውን በመሸጥ ብድሩን መመለስ ያልቻለበትን ምክንያት አልገለጸም በሚል እና ብድሩም በተጠሪዎች በየ3 ወሩ የሚከፈል ሆኖ ክፍያውን ያቋረጡ ሆኖ እያለ ብድሩን ለማጠናቀቅ የመክፈያ ጊዜ አልደረሰም በሚል ፍ/ቤቱ ክሱን ውድቅ ያደረገበትን አግባብ ለመመርመር ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡1ኛ ተጠሪ በቀን 05/07/2014ዓ.ም የተጻፈ መልስ የስር ክርክር በማጠናከር የስር ፍርድ ቤት ብይን ተገቢ ነዉ የሚሉበትን ምክንያት በዝርዝር አቅርበዋል፡፡2ኛ ተጠሪ ፍርድ ቤቱን መጥሪያ ተቀብሎ መልስ ባለማቅረቡ መብቱ ታልፏል፡፡አመልካች አቤቱታዉን በማጠናከር መልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ተባለበትን ጭብጥ መሰረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉ ለክሱ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ የባንክ ብድር አመላለስ ሚመለከት ነዉ፡፡የአመልካች የዳኝነት ጥያቄም ተጠሪዎች ብድሩን በዉሉ መሰረት ጊዜን ጠብቀዉ እየከፈሉ አይደለም በሚል ቀሪዉን እዳ ከወለድና ቅጣት ጋር እንዲከፍሉ ዳኝነት መጠየቁን ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪዎች

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በበኩላቸዉ ባንኩ በመያዣ የያዘዉን ንብረት መሸጥ ሲችል ክስ ማቅረቡ ተገቢነት የለዉም የሚል መከራከሪያ በማቅረባቸዉ ፍርድ ቤቱም ይህንኑ እና ሌሎች መከራከሪያዎችን እንደመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በመዉሰድ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 245(2) ምርኩዝ በማድረግ መዝገቡን መዝጋቱን በቀን 08/03/2014ዓ.ም የሰጠዉ ብይን ይዘት ያሣያል፡፡በዚህ ብይን የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን እንደሚከለተዉ መርምረናል፡፡

በመሰረቱ ክስ ወይም የክስ መዝገብ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ምክንያት ሊዘጋ የሚችለዉ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ሆኖ ሊቀርቡ ይችላሉ ተብሎ ከተዘረዘሩት ምክንያቶች አንዱ መኖሩ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡(የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 244(2) ይመለከቷል)፡፡የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስረጃ የተደገፈና ተገቢ ሆኖ ከተገኘ እና ፍርድ ቤቱም ከተቀበለ ክርክሩን ይቋረጣል ማለት ነዉ፡፡ነገር ግን የከሳሹ መብት የሚወሰነዉ ተቀባይነት ባገኘዉ መቃወሚያ ዓይነት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 245(2) ድንጋጌ ይዘት ያሣያል፡፡ይኸዉም ጉዳዩ አስቀድሞ ዉሳኔ ያገኘ መሆኑ፣ክሱ በይርጋ የታገደ መሆኑ ወይም በእርቅ ስምምነት የተፈጸመ መሆኑ ከተረጋገጠ ክሱን በመዝጋት (dissimisal of the suit) የሚያስከትል ሲሆን እንዲህ በሆነ ጊዜ ጉዳዩ እልባት እንዳገኘ ስለሚቆጠር ከሳሹ በዚህ ጉዳይ ሌላ ክስ ለማቅረብ አይችልም፡፡በሌሎች መቃወሚያዎች መዝገቡን መዝጋት (srike out the suit) የሚኖረዉ ዉጤት ግን ከዚህ የተለየ ነዉ፡፡በዚህ ጊዜ ከሳሹ ተገቢዉን ስርዓት አሟልቶ በጉዳዩ ላይ ክስ የማቅረብ መብቱን የሚያስቀር አይደለም፡፡በዚህ ረገድ እንደማሳያ ሊጠቀስ የሚቻለዉ ክስ የቀረበለት ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን የለዉም ተብሎ የክስ መዝገቡ ቢዘጋ ስልጣን ላለዉ ፍርድ ቤት ክስ የማቅረብ  መብቱን የሚያስቀር አለመሆኑ ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ክስ መዝገብ የዘጋበት አንደኛዉ ምክንያት ባንኩ በመያዣ የያዘዉን ንብረት ሳይሸጥ ወይም መሸጥ ያልቻለበትን ምክንያት ሳያስረዳ ክስ ማቅረብ አይችልም የሚል ነዉ፡፡በመሰረቱ ይህ መከራካሪያ በዓይነቱ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ተብሎ የሚቀርብ ሳይሆን ክሱ የክስ ምክንያት አለዉ ወይስ የለዉም የሚለዉ ጋር ተይይዞ የሚታይ ነዉ፡፡ይሁንና አመልካች በመያዣ የያዘዉን ንብረት ሳይሸጥ ክስ ማቅረብ ይችላል ወይስ አይችልም የሚለዉን ጭብጥ በሚመለከት ይህ ሰበር ችሎት ከዚህ ቀደም ዉሳኔ የሰጠበት ጉዳይ ነዉ፡፡

በመሰረቱ ባንክ በመያዣ የያዛቸውን ንብረቶች የፍርድ ሂደትን ማለፍ ሳያስፈልግ በሐራጅ የመሸጥ ህጋዊ መብት ያለው መሆኑን አዋጅ ቁጥር 97/90፣ 98/90 እና 216/92 የሚያስገነዝቡ ናቸዉ፡፡ የአዋጁ አይነተኛ ዓላማ ባንኮች በተቻለ ፍጥነት በብድር የሠጡትን ገንዘብ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በመሰብሰብ እንደገና መዋዕለ ንዋዩን ለኢንቨስትመንት ስራ እንዲውል በማድረግ በአገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ አዎንታዊ ሚና መጫወት ነው፡፡ባንኮች በራሳቸው ምርጫ በብድር የሰጡትን ገንዘብ የመሰብሰብ ተግባር እንዲከተሉ አስገዳጅ መንገድ ስለመሆኑ የሚያሳይ ድንጋጌ አለመያዙን፤ በሌላ አገላለጽ ባንኮች ብድራቸውን ለማስመለስ በፍርድ ቤት በኩል ክስ ሲመሰርቱ ጉዳዩ በአዋጅ መሰረት ሊፈጸም ይገባል ሊባል የማይችል መሆኑን እና መያዣ ንብረቶች ላይ ከአዋጁ ባገኙት መብት መሰረት እንቅስቃሴ ማድረግ ወይም አለማድረግ ክስ ከማቅረብ የሚያግዳቸዉ አለመሆኑን ያስገነዝባል፡፡ባንኮች በራሳቸው ምርጫ በብድር የሰጡትን ገንዘብ የመሰብሰብ ተግባር ሳይፈጽሙ በፍርድ ቤት ክስ ቢመሰርቱ ወይም በመረጡት መንገድ የመሄድ ሁኔታ አዋጁ ከወጣበት ዓላማ ጋር ሊፃረር ይችላል ተብሎ የሚታሰብ አለመሆኑን የሰበር ችሎቱ ዉሳኔ ይዘት ያሣያል፡፡ስለሆነም ባንኮች በአዋጁ የተሠጣቸውን ሥልጣን በመተው ወይም እንቅስቃሴውን ጀምረው እያለም ቢሆን በፍርድ ቤት ክስ ቢመሰርቱ ተቀባይነት የለውም ወይም በቅድሚያ የያዘዉን ንብረት መሸጥ አለበት የሚባልበት ህጋዊ መሰረት የለም፡፡በዚህም ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 244(2) ለክርክሩ አግባብነት የሌለዉ ከመሆኑም ባሻገር አስገዳጅ ሰበር ችሎት ዉሳኔ የሚቃን ነዉ፡፡(ሰበር መ/ቁ/44164 ቅጽ 10 ላይ የታተመዉን ይመለከቷል)፡፡

ሌላኛዉ የስር ፍርድ ቤትዉሳኔ ምክንያት የክፍያ መጨረሻ ወይም ማጠናቀቂያ ጊዜ ሳይደርስ የቀረበ ክስ ነዉ የሚል ሲሆን የአመልካች ክስ ፍሬነገር የሚያሳዉ ተጠሪዎች ክፍያዉን ጊዜ ጠብቀዉ እየከፈሉ አይደለም በተከታታይ ጊዜ አቋርጠዋል የሚል ሲሆን ተጠሪዎችም ክፍያ ማቋረጣቸዉን ሳይክዱ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት እንዳጋጠማቸዉ ገልጸዉ መከራከራቸዉን መዝገቡ ያሣያል፡፡ክሱ የቀረበዉ የብድር ዉል መሰረት አድርጎ እንደመሆኑ አከፋፈሉን በሚመለከት በዉሉ የተስማማሙበት ሁኔታ ካልተከበረ በጉዳዩ የዉል ግዴታ ጥሰት ተፈጽሟል የሚል ወገን እንደዉሉ እንዲፈጸምለት ክስ የማቅረብ መብት የሚሰጠዉ ስለመሆኑ ከዉል ህጎች የምንገነዘበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡(የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1771 ይመለከቷል)፡፡ስለሆነም ተጠሪዎች ክፍያ ማቋረጥ አለማቋረጣቸዉ እና ህጋዊ ዉጤቱ የግራቀኙን ዉል እና አግባብነት ያለዉ ህግ በማገናዘብ እልባት የሚሰተዉ እንጂ ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ለማቋረጥ የሚያስችል የህግ ምክንያት ባለመኖሩ በዚህ ረገድም የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ስህተት ሆኖ አግኝተናል፡፡

የመጨረሻዉ የቅሬታ ነጥብ 2ኛ ተጠሪ ከክሱ መሰናበቱ ተገቢ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነዉ፡፡በዚህ ረገድ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረዉ 2ኛ ተጠሪም ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ተበዳሪ ነዉ በማለት ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዉ የተከሰሰዉ የ1ኛ ተጠሪ ባል በመሆኑ ብቻ እንጂ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተበዳሪ ወይም ዋስ አይደለም የሚል ምክንያት ጠቅሶ ነዉ ያሰናበተዉ፡፡በእርግጥ አከራካሪዉን ፍሬነገር መመርመር እና በማስረጃ አጣርቶ የመወሰን ስልጣን የስር ፍርድ ቤቶች መሆኑ እሙን ነዉ፡፡ይሁንና ፍርድ ቤቱ ከድምዳሜ ሊደርስ የሚገባዉ በጉዳዩ ላይ የቀረበዉን ማስረጃ መርምሮና አመዛዝኖ መሆን አለበት፡፡በዚህ ጉዳይ ግን ፍርድ ቤቱ 2ኛ ተጠሪን የሚያስከስስ የህግ ወይም የዉል ምክንያት መኖር አለመኖሩን የአመልካችን ማስረጃ መርምሮ ስለማረጋገጡ ዉሳኔዉ በዝርዝር አያሣይም፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ ጉዳዩ አሁንም በማስረጃ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባዉ እንደሆነ ያመላክታል፡፡ስለዚህም በዚህም ረገድ ፍርድ ቤቱ ድምዳሜ በማስረጃ የተደገፈ ባለመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ሆኖ አግኝተናል፡፡

ሲጠቃለል አመልካች በመያዣ የያዘዉን ንብረት ሳይሸጥ ወይም መሸጥ ያልቻለበትን ምክንያት ሳይገልጽ ክስ ማቅረብ አይችልም በሚል እና በሌሎች ስነስርዓታዊ ምክንያት የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 245(2) በመጥቀስ የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉ ብይን በተመሳሳይ ጉዳይ ሰበር ችሎቱ የሰጠዉን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን በመሆኑ በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ2(4/ሸ) እና 10(1/ሠ) መሰረት በዚህ ሰበር ችሎት ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ዉሳኔ</u>

1ኛ/የሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/15053 ላይ ቀን 08/03/2014ዓ.ም የሰጠዉን ብይን እና ይህንኑ በማጽናት የደቡብ ምዕ/ኢ.ት/ ህ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ10222 ላይ በቀን 30/03/2014ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ/ፍርድ ቤቱን የዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍሬነገሩ ላይ ግራቀኙን አከራክሮ እና አጣርቶ ተገቢዉን ዉሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 341(1) መሰረት ለሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መልሰናል፡፡

3ኛ/በዚህ ችሎት የተደረገ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡ይጻፍ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*